# ለጥቅማጥቅሞችለማመልከትምንእንደሚያስፈልግዎ:
# የቤተሰብ እረፍት

ለጥቅማጥቅሞችለማመልከትለመዘጋጀትየሚያግዝዎትንይህንንዝርዝርይጠቀሙ።

## ሽፋን ለማግኘት የመሰረጡ ሰራተኞች እና የራሳቸውን ስራ የሚሰሩ ሰዎች የሚከተለውን ማድረግ ይችላሉ፡

- የ Frances Online መለያ/አካውንት ይፍጠሩ
- በFrances Online መለያቸውበኩልበአንላይንለጥቅማጥቅሞችማመልከት
- ለጥቅማ ጥቅሞች በመልዕክት ወይም በስልክ ማመልከት:
  - የማመልከቻ ቅጹን ከ የሚከፈልበት እረፍት ድረገጽ ላይ ማውረድ እና ፕሪንት ማድረግ
  - 833-854-0166 (ከክፍያ ነጻ) ለእኛ መደወል

Frances Online ለሚከፈልበት እረፍት ለማመልከት **ፈጣኑ እና ቀላሉ መንገድ** ነው። Frances Onlineን ማግኘት ካልቻሉ የማመልከቻ ቅጹን ከድረገጻችን ላይ ማውረድ እና ለማመልከት ለእኛ በመልዕክት መላክ ወይም በስልክ ቁጥር 833-854-0166 መደወል ይችላሉ። የሚያመለክቱት በወረቀት ወይም በስልክ ከሆነ ምላሽ ለማግኘት ረጅም ጊዜ ሊወስድብዎ ይችላል።

እርስዎን ወክሎ የተመደበ ተወካይ ቅጽንበመሙላት ለሚከፈልበት እረፍት ጥቅማ ጥቅሞች የሚያመለክትልዎ ሰው ሊኖርዎት ይችላል። እባክዎ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሰራተኛ መመሪያን ይመልከቱ።

በኦሬጎን የሚከፈልበት እረፍት/ Paid Leave Oregon / ላይ ከመሳተፍ ይልቅ አሰሪዎ ተመጣጣኝ ዕቅድ ካለው በዛ ተመጣጣኝ ዕቅድ ስር የተለየ ማመልከቻ ማስገባት አለብዎ። ይህንእንዴትማድረግእንዳለብዎትመመሪያዎችእንዲሰጥዎአሰሪዎ ንይጠይቁ።

## ይዘጁ

**ከማመልከትዎበፊት፡-**

- ☐ ለአሰሪዎያሳውቁ — የእረፍትጊዜዎከመጀመሩ 30 ቀናትበፊትለአሰሪዎመንገርአለብዎት። ለድንገተኛ ሁኔታ የ24 ሰዓት የቃል ማስታወቂያ ሊሰጧቸው እና ከዚያም በ3 ቀናት ውስጥ የጽሁፍ ማስታወቂያ እስኪደርስዎ ሊከታተሉ ይችላሉ። ማስታወቂያ መስጠት ካልቻሉ ሌላ ሰው ይህን ሊያደርግልዎ ይችላል።

  **ማስታወሻ፡-** ስለ ዕረፍትዎ ለአሰሪዎ እንደነገሩት ማሳየት ካልቻሉ የሚከፈልበት እረፍት/ Paid Leave/ የመጀመሪያውን ሳምንታዊ የጥቅማ ጥቅም ክፍያዎን በ25% ሊቀንስብዎ ይችላል።
- ☐ የሚፈልጉትንመረጃ - የእያንዳንዱእርምጃዝርዝሮችአንድላይተሰብስበውበዚህዝርዝርውስጥተካትተዋል።
- ☐ የFrances Online የጠያቂ መለያ/አካውንት ይፍጠሩ — Frances Online ለጥቅማ ጥቅሞች ለማመልከት ፈጣኑ መንገድ ነው። የሚሰሩት የራስዎን ስራ ከሆነ ይህ የጠያቂ መለያ/አካውንት ሁለተኛ መለያ/አካውንት ነው። ይህ ሽፋን ለማግኘት ለማመልከት ከፈጠሩት የአሰሪዎ መለያ/አካውንት ጋር አንድ አይነት አይደለም።

## እርምጃ 1፡- የFrances Online አካውንትይፍጠሩ

**መለያለመፍጠርየሚያስፈልግዎነገር፡-**

- ☐ ሙሉህጋዊስምዎእናየትውልድቀንዎ።
- ☐ የማህበራዊዋስትናቁጥርዎ (SSN) ወይምየግልየግብርከፋይመለያቁጥርዎ (ITIN)።
- ☐ ስልክቁጥርዎን፣ የኢሜይል አድራሻዎን፣ አካላዊ አድራሻዎን እና ከአካላዊ አድራሻዎ የተለየ ከሆነ፣ የመልዕክት አድራሻዎን ጨምሮ የግንኙነት መረጃዎ።
- ☐ የስቴትዎመንጃፍቃድወይምየስቴትመታወቂያካርድ (ካለዎት)።

- ☐ የኢሜይል አድራሻዎ።
- ☐ ቀደም ሲል ለሚከፈልበት እረፍት ወይም የስራ አጥነት መድን/Unemployment insurance ዕቅድ ጥያቄ አስመዝግበው ከሆነ መለያዎን/አካውንትዎን በአስተማማኝ ሁኔታ ለማስተካከል ደብዳቤ እንድንልክልዎ እኛ ልናስፈልግዎት እንችላለን።

## እርምጃ 2፡- ለጥቅማጥቅሞችያመልክቱ

**በፍራንሲስኦንላይንላይመለያከፈጠሩበኋላወዲያውኑማመልከትይችላሉ። ለማመልከት ለFrances Online ይመዝገቡ።**

### ለማመልከትምንእንደሚያስፈልግዎ፡-

- ☐ በFrances Online በኩል የሚያመለክቱ ከሆነ የተጠቃሚ ስምዎ እና የይለፍ ቃልዎ።
- ☐ የማህበራዊዋስትናቁጥርዎ (SSN) ወይምየግልየግብርከፋይመለያቁጥርዎ (ITIN)።
- ☐ የሚያመለክቱበት እረፍት አይነት።
- ☐ የጠየቁትየዕረፍትመርሃግብር (ተከታታይአሊያምጊዜያዊ) እናየሚከፈልበትየእረፍትጊዜየሚጠበቁትየመጀመሪያእናየመጨረሻቀናት።
    - ተከታታይእረፍትማለትእረፍትዎከሚጀምርበትቀንእስከሚያበቃበትቀንድረስበመካከሉባለውጊዜውስጥምን ምአይነትስራሳይሰሩእረፍትዎንሲወስዱነው።
    - የተቆራረጠ እረፍት ማለት በእረፍትዎ የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ቀናት መካከል የቀናት ወይም ሳምንታት እረፍት ሲወስዱ ነገር ግን በእረፍትዎ ላይ እያሉም ሲሰሩ ነው። የተቆራረጠ እረፍት መውሰድ ያለብዎ ለሁለት ወይም ከዚያ በላይ የኑሮ ሁኔታዎች በተመሳሳይ ጊዜ እረፍት ሲወስዱ ወይም ለቅድመ ምደባ እረፍት ሲያመለክቱ ብቻ ነው።
- ☐ የአሁኑእናያለፉት 18 ወራትየስራመረጃዎየሚከተሉትንጨምሮ፡-
    - የአሰሪ የንግድ ድርጅት ስም፣ አድራሻ እና ስልክ ቁጥር
    - የአሰሪዎ የንግድ ድርጅት መለያ ቁጥር (BIN) ወይም የፌደራል የአሰሪ መለያ ቁጥር (FEIN) (እነዚህን ቁጥሮች ከአሰሪዎ ያረጋግጡ)
    - የስራመደብዎመጠሪያ (ስራዎትንለማግኘትእንዲረዳዎ)
    - የተቀጠሩበትቀን
    - በአሰሪዎ በየ ምን ያክል ጊዜ ይከፈልዎታል
    - አሰሪዎ ምን ያክል ይከፍልዎታል
    - አብዛኛውንጊዜለእያንዳንዱአሰሪየሚሰሩትበየሳምንቱየቀናትብዛት
    - ስለእረፍትዎለአሰሪዎየነገሩበትቀን
- ☐ ሊያገኙት የሚችሉት የሰራተኞች የክፍያ ጊዜ ክፍያ ማጣት ጥቅማ ጥቅሞች ወይም የስራ አጥነት መድን/Unemployment insurance ፕሮግራም ጥቅማ ጥቅሞችን የተመለከተ መረጃ።
- ☐ ስላሉዎትማንኛውምተመጣጣኝየእቅድሽፋንእናበዚህዕቅድስርስለወሰዱትየትኛውምከክፍያጋርየሚሰጥእረፍትየተመለ ከተመረጃ።
- ☐ ጥቅማጥቅምዎየሚከፈልበትየሚመርጡበትዘዴ። በቅድሚያከተከፈለየዴቢትካርድእናቀጥተኛተቀማጭመካከልመም ረጥይችላሉ። ቀጥተኛተቀማጭገንዘብከመረጡ፣የባንክሒሳብዎንእናየማስተላለፊያቁጥሮችያስፈልግዎታል።
- ☐ የግብርተቀናሽምርጫዎ።

## እርምጃ 3፡- የማንነት ማረጋገጫ

ማመልከቻዎ ከደረሰን በኋላ ማንነትዎን እናረጋግጣለን። አንዳንድ ጊዜያት ማንነትዎን ለማረጋገጥ ተጨማሪ መረጃ ልንፈልግ እንችላለን። መለያዎን/አካውንትዎ በሚከፍቱበት ወቅት የኢሜይል ማስታወቂያዎች ለማግኘት መርጠው ቢሆንም እንኳ በዩ.ኤስ መልዕክት ደብዳቤ እንልክልዎታለን። **እባክዎ የዩ.ኤስ መልዕክትን ይመልከቱ** እና ሊኖሩን ለሚችሉ ለየትኛውም የክትትል ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ዝግጁ ይሁኑ።

## እርምጃ 4፡- የአኗኗር ሁኔታዎን ማረጋገጥ

**የህይወትክስተትዎንለማረጋገጥየሚያስፈልግዎነገር**

በFrances Online መለያዎ/አካውንትዎ ላይ ስለ ጥያቄዎ በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ የሚጠይቅዎ መጠይቅ ይኖራል። ወደ Frances Online መለያዎ/አካውንትዎ መግባት እና መጠይቁን ማጠናቀቅ ይኖርብዎታል። በተጨማሪም ብቁ የሚያደርግ የአኗኗር ሁኔታዎን ለማረጋገጥ ሰነዶችዎን (ከታች ተዘርዝረዋል) እንዲልኩልን እንጠይቅዎታለን። ይህን ለማድረግ ቀላሉ መንገድ ለጠያቂዎች መለያ/አካውንት ይህን በFrances Online easiest ላይ ካለው መልዕክት ጋር አብሮ መላክ ነው። የFrances Online መለያ/አካውንት ከሌለዎ የማረጋገጫ ሰነዶችዎን ከወረቀት ማመልከቻዎ ጋር በመልዕክት ይልኩልናል። በተጨማሪም ተፈላጊውን መረጃ ለማግኘት ልንደውልልዎ እችላለሁ።

የምንጠይቃቸው የማረጋገጫ ሰነዶች እርስዎ እንደሚፈልጉት የእረፍት አይነት ላይ ይመሰረታል። ከታች ከተዘረዘሩት ሰነዶች ውስጥ አንዱን ሰነድ ለእኛ መስጠት አለብዎ። ይህ ሰነድ እረፍትዎን ለማረጋገጥ ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎች የማያካትት ከሆነ ተጨማሪ መረጃ ልንጠይቅዎ እንችላለን።

በዚህ ዝርዝር ላይ የተገለጹት ሰነዶች በጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ወይም የቤተሰብዎ አባል የጤና እንክብካቤ አቅራቢ መሞላት ያለባቸው ክፍሎች ሊኖሯቸው ይችላሉ።

### ከወሊድ በኋላ በመጀመሪያው ዓመት ውስጥ ልጅን ለመንከባከብና ቁርኝት ለመፍጠር የሚወሰድ የቤተሰብ እረፍት:

በመንግስት ተቋም ካልተሰጠ በስተቀር የማረጋገጫ ሰነድዎ የሰጪውን የመጀመሪያና የመጨረሻ ስም፣ ኃላፊነት ወይም ልዩ ሙያ፣ የግንኙነት መረጃ፣ የእጅ ጽሁፍ ወይም የኤሌክትሮኒክስ ፊርማ፣ እና ሰነዱ የተፈረመበት ወይም የተሰጠበትን ቀን መያዝ አለበት። ሊጠቀሟቸው የሚችሏቸው የማረጋገጫ ሰነዶች የሚከተሉት ናቸው:

- የልጅዎ ኦፊሴላዊ የልደት የምስክር ወረቀት።
- የወሊድ ቅጽ የሚከፈልበት እረፍት የኦሬጎን ማረጋገጫ ። ይህ የተሰጠው ልጁ ከመወለዱ በፊት ከሆነ ልጁ እንደሚወለድ ከሚጠበቅበት ቀን በፊት በ60 ቀናት ውስጥ ቀን የተጻፈበት እና የተፈረመ መሆን አለበት።
- ለውጭአገርውልደትየቆንስላሪፖርት።
- አባትነት ወይም ሞግዚትነትን የሚገልጽ በፍርድ ቤት የተሰጠ ሰነድ።
- በሆስፒታል ተወካይ ተፈርሞ የተረጋገጠ እና ልጅዎ በተወለደ በ5 ቀናት ውስጥ የተፈረመ በፍቃደኝነት የተሞላ የአባትነት ማረጋገጫ።
- በልጅዎወይምየነፍሰጡርወላጅየጤናእንክብካቤአቅራቢየተሰጠሰነድ። ነፍሰ ጡሯ ወላጅ እርስዎ ወይም ሌላ ወላጅ ልትሆኑ ትችላላችሁ፣ ነገር ግን ሰነዱ እርስዎን እንደ የልጁ ወላጅ መጥቀስ አለበት። ይህ የተሰጠው ልጁ ከመወለዱ በፊት ከሆነ ልጁ እንደሚወለድ ከሚጠበቅበት ቀን በፊት በ60 ቀናት ውስጥ ቀን የተጻፈበት እና የተፈረመ መሆን አለበት። ስለዚህ ሰነድ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሰራተኛ መመሪያውን ይመልከቱ።
- ከልጅዎወሊድጋርተያያዥየሆስፒታልምዝገባቅጽ።

ከእርግዝና ጋር ተያያዥነት ላለው **ተጨማሪ የሁለት ሳምንታት እረፍት** በአሁኑ ወቅት ነፍሰ ጡር እንደሆኑ ወላጅ ወይም እረፍትዎ ከመጀመሩ በፊት ባለው ዓመት ውስጥ እንደወለዱ ከልጁ ጋር ያልዎትን ዝምድና የሚያሳይ ሰነድ ያስፈልግዎታል።

## ከጉዲፈቻ ወይም የማደጎ እንክብካቤ ምደባ በኋላ በመጀመሪያው ዓመት ውስጥ ልጁን ለመንከባከብ እና ቁርኝት ለመፍጠር የሚወሰድ የቤተሰብ እረፍት:

በመንግስት ተቋም ካልተሰጠ በስተቀር የማረጋገጫ ሰነድዎ የሰጪውን የመጀመሪያና የመጨረሻ ስም፣ ኃላፊነት ወይም ልዩ ሙያ፣ የግንኙነት መረጃ፣ የእጅ ጽሁፍ ወይም የኤሌክትሮኒክስ ፊርማ፣ እና ሰነዱ የተፈረመበት ወይም የተሰጠበትን ቀን መያዝ አለበት። ሊጠቀሟቸው የሚችሏቸው የማረጋገጫ ሰነዶች የሚከተሉት ናቸው:

- የልጅዎንምደባየሚያረጋግጥየፍርድቤትትእዛዝኮፒ።
- እንደየማደጎወይምየጉዲፈቻወላጅነትከወከልዎጠበቃየተሰጠየልጅዎንምደባየሚያረጋግጥየተፈረመደብዳቤ።
- በልጅዎምደባላይተሳታፊበሆነየማደጎእንክብካቤ፣ የጉዲፈቻድርጅትወይምበማህበራዊሰራተኛየተሰጠምደባውንየሚያረጋግጥሰነድ።
- ለልጅዎበዩናይትድስቴትስየዜግነትናየኢሚግሬሽንአገልግሎቶች (USCIS) የተሰጠሰነድ።

## ከባድየጤናሁኔታያጋጠመውንየቤተሰብአባልለመንከባከብየሚወሰድየቤተሰብእረፍት:-

በጤና እንክብካቤ አቅራቢ የተሰጠ የቤተሰብዎ አባልን ከባድ የጤና ሁኔታ የሚያሳይ ማረጋገጫ ማሳየት ይኖርብዎታል።

ሊጠቀሟቸው የሚችሏቸው የማረጋገጫ ሰነዶች የሚከተሉት ናቸው:

- የሚከፈልበት እረፍት የኦሬጎን የከባድ የጤና ሁኔታ ማረጋገጫ ቅጽ
- የኦሬጎን እና የፌደራል የቤተሰብና የህክምና እረፍት የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ማረጋገጫ/ የምስክር ወረቀት
- የቤተሰብና የህክምና እረፍት ህግ (FMLA) ስለ ሰራተኛው የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ማረጋገጫ/ የምስክር ወረቀት የከባድ የጤና ሁኔታ ቅጽ
    - ማስታወሻ:- የዩ.ኤስ የአሰሪና ሰራተኛ መምሪያ ይህን ቅጽ ይሰጣል። በተጨማሪም ለከባድ የጤና ሁኔታ የአሰሪዎን የFMLA ማረጋገጫ/የምስክር ወረቀት እትም መጠቀም ይችላሉ።
- በጤና እንክብካቤ አቅራቢ የተሰጠ ሰነድ
- ሌላ ሰነድ — ለተፈላጊ ሰነዶች ዝርዝር የሰራተኛ መመሪያውን ይመልከቱ።

ሰነድዎ የሚከተለውን መረጃ መያዝ አለበት:

- የመጀመሪያናየመጨረሻስምዎ
- የትውልድቀንዎ
- ከባድ የጤና ሁኔታው እንደጀመረ ወይም የእረፍት ፍላጎት እንደፈጠረ የሚገመትበት ቀን
- ሁኔታው የሚቆይበት ወይም የማገገሚያ ጊዜዎ አሳማኝ ግምት
- የተቆራረጠ እረፍት ድግግሞሽና የቆይታ ጊዜ አሳማኝ ግምት እና ተግባራዊ ከተደረገ የተገመተ የህክምና የጊዜ ሰሌዳ
- የቤተሰብዎ አባል ከባድ የጤና ሁኔታ እንዳለበት የሚገልጽ የምርመራ ወይም ሌላ መረጃ

የማረጋገጫ ሰነድዎ በተጨማሪም እርስዎን እንደ የታካሚው የቤተሰብ አባል በመጀመሪያና የመጨረሻ ስምዎ መግለጽ አለበት። ሰነድዎ በእርስዎና በታካሚው መካከል ያለውን የቤተሰብ ዝምድና የማያሳይ ከሆነ ከሚከተሉት ሰነዶች ውስጥ ቢያንስ አንዱን መላክ አለብዎ፡

- ህጋዊ የጋብቻ ምስክር ወረቀት
- የተረጋገጠ የቤት ውስጥ አኗኗሪነት መግለጫ
- ህጋዊ የልደት የምስክር ወረቀት

- አንድ ወይም ከዚያ በላይ በገለልተኛና ሊረጋገጥ በሚችል ሶስተኛ ወገን የተሰጡ ጋብቻን፣ የቤት ውስጥ አኗኗሪነትን ወይም በእርስዎና በታካሚው መካከል ያለውን መሰረታዊ የቤተሰብ ግንኙነት የሚገልጹ ሰነዶች። ሰነዱ እረፍትዎን ከመጀመርዎ በፊት በስድስት ወራት ውስጥ የተሰጠ መሆን አለበት።

**ልጅ በጉዲፈቻ ወይም በማደጎ እንክብካቤ ወደ ቤተሰብዎ ለመቀበል አስፈላጊ የሆነ ለተተኪ ስራዎች የሚወሰድ የቤተሰብ እረፍት፡**

ማረጋገጫዎ የጠየቁትን እረፍት ከሚወስዱበት ቀን በፊት ከ180 ባልበለጡ ቀናት ውስጥ ቀን የተጻፈበት መሆን አለበት።

ሰነዱ የሚከተለውን ማሳየት አለበት:

- እንደታሰበ የማደጎ ወይም የጉዲፈቻ ወላጅ የመጀመሪያ ስምዎን እና የመጨረሻ ስምዎን
- የልጁን የመጀመሪያና መጨረሻ ስም
- የልጁን የትውልድ ቀን።
- ሰነድዎ በመንግስት ተቋም ካልተሰጠ በስተቀር የሰጪውንየመጀመሪና መጨረሻ ስም መያዝ አለበት
    - ኃላፊነት ወይም ልዩ ሙያ
    - እንደ የመልዕክት አድራሻ፣ ኢሜይል ወይም ስልክ ቁጥር ያሉ የግንኙነት መረጃዎች፣ የሰጪው የእጅ ጽሁፍ ወይም የኤሌክትሮኒክስ ፊርማ
    - ሰነዱ የተፈረመበት ቀን።

ሊጠቀሟቸው የሚችሏቸው ሰነዶች የሚከተሉት ናቸው:

- የፍርድ ቤት ትእዛዝ ግልባጭ።
- የማደጎ ወይም የጉዲፈቻ ወላጁን በሚወክል ጠበቃ የተፈረመ ደብዳቤ።
- በየማደጎ እንክብካቤ፣ የጉዲፈቻ ድርጅት፣ ወይም በምደባው ላይ በተሳተፈ ማህበራዊ ሰራተኛ የተሰጠ ሰነድ።
- በዩናይትድ ስቴትስ የዜግነትና የኢሚግሬሽን አገልግሎቶች ለልጁ የተሰጠ ሰነድ

**በFrances Online በኩል ለጥቅማ ጥቅሞች እንዴት እንደሚያመለክቱ በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎ ለጥቅማ ጥቅሞች እንዴት እንደሚያመለክቱ የዋና ዋና ሀሳቦች ቪዲዮን በ paidleave.oregon.gov ይመልከቱ።**

ለጥቅማ ጥቅሞች ስለማመልከት በተመለከተ ተጨማሪ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት የእኛን የሰራተኛ መመሪያ ፣ የራሳቸውን ስራ የሚሰሩ ሰዎች መመሪያያንብቡ፣  ዉም paidleave.oregon.govን ይጎብኙ።